TB Contact Investigations Amharic

Minnesota Department of Health

# የነቀርሳ ተላላፊነት ምርመራዎች

**የነቀርሳ ተላላፊነት ምርመራ ምንድን ነው?**
አንድ ሰው የነቀርሳ በሽታ ሲይዘው በሽታው ወደ ሌሎች ሰዎች ተላልፎ መሆኑን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሠራተኞች በሽታው መተላለፉን ለማወቅ የሚያደርጉት ምርመራ የተላላፊነት ምርመራ ተብሎ ይጠራል።

ነቀርሳ የያዘው ሰው ሳያውቀው በሽታውን ለሰው ሊያጋባ ይችላል። ነቀርሳ ወደ ሌላ ሰው ከተጋባ ያ ሰው እንዳይታመም ሕክምና ያስፈልገዋል።

በተላላፊነት ምርመራ ጊዜ ለጤና ጥበቃ ሠራተኛው የሚሰጡት መረጃ በምሥጢር የሚያዝ ነው። የርስዎ መረጃ ሌላ ሰው እንዳያየው ሁልጊዜ የተጠበቀ ይሆናል።

**የነቀርሳ ተላላፊነት ምርመራ እንዴት ይኪያሄዳል?**
የጤና ጥበቃ ሠራተኛው ሳል ወይም ሕመም የጀመርዎት መቼ እንደሆነ ይጠይቅዎታል/ትጠይቅዎታለች። ሕመሙ ከጀመርዎት ጊዜ ጀምሮ አብረው ያሳለፉትን ሰው **በሙሉ** ለማስታወስ ይሞክሩ ማለትም ቤትዎ አብረው የሚኖሯቸው ሰዎች፣ቤትዎ የሚመጡ እንግዶች፣ ልጆች፣ጓደኞች፣የሥራ ባልደረቦች፣የትምህርት ክፍል ጓደኞች እንዲሁም ልጅ ጠባቂዎች። ሕመም እስከጀመርዎት ጊዜ ድረስ ሳምንታት ወይም ወራት ወደ ኋላ ያስቡ። ከዛም በኋላ የጤና ጥበቃ ሠራተኛዉ/ዋ ለነቀርሳ ማን ማን መመርመር እንዳለበት ይወስናል/ትወስናለች።

**ለጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ የሚነግሩት መረጃ ሁሉ <u>የግልና ማንም ሰው የማያየው</u> ይሆናል።** እርስዎ ፈቃደኛ ካልሆኑ በስተቀር የጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ ስምዎንም ሆነ ሌላ መረጃ ለማንም ሰው አይነግርም/አትነግርም። ይህም ማለት ለጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ሠራተኛዋ ሐቀኛ መረጃ መስጠት ይችላሉ።

የጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ የቤትዎንም ሆነ የሌሎች ጊዜ የሚያሳልፉበትን ቦታዎች አየር ሄዶ/ሄዳ ማየት ይኖርበታል/ይኖርባታል። ይህም ማን የነቀርሳ ምርመራ ማድረግ እንዳለበት ለመወሰን ይረዳል።

የጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ ሰዉ የነቀርሳ ቆዳ ምርመራ እንዲያገኙ ያደርጋሉ እንጂ ማን ነቀርሳ እንደያዘው አይናገሩም። ከእርስዎ ጋር ብዙ አብረዎት የነበሩት ሰዎች መጀመሪያ ይመረመራሉ።

የነቀርሳ ተላላፊነት ምርመራዎች ጊዜ ይፈጃሉ። የጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ የቆዳ ምርመራ የሚያስፈልገው ሰው ሁሉ ምርመራውን ማግኘቱን ማረጋገጥ ይፈልጋል/ትፈልጋለች። በዚህ ምክንያት የጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ ጥያቄዎቹን ከአንድ ጊዜ በላይ ደግመው ሊጠይቅዎት/ልትጠይቅዎት ይችላል። የተለዩ ጥያቄዎች ወደፊት ለጠየቁ ይችላሉ። ይህንንም የሚያደርጉት መረጃውን ሁሉ በደንብ ማገናዘብ እንዲቻል ነው። አሁንም ያስታውሱ፦ ለጤና ጥበቃ ሠራተኛው የሚነግሩት <u>መረጃ ሁሉ በምሥጢር የሚያዝ ነው</u>።

**ሰዎች ነቀርሳ የሚይዛቸው እንዴት ነው?**
**ማንኛውም ሰው ነቀርሳ ሊይዘው ይችላል።** የሳንባ ነቀርሳ የያዘው ሰው በሚስልበት ወይም በሚያስነጥስበት ጊዜ ጥቃቅን የነቀርሳ ጀርሞች በአየር ውስጥ ሊያሠራጭ ይችላል።



የሳንባ ነቀርሳ ከያዘው ሰው ጋር በቅርብ ሆነው ጊዜ ቢያሳልፉ የነቀርሳ ጀርሞቹን ተንፍሰው ወደ ራስዎ ሳንባ ሊያስገቡ ይችላሉ። ነቀርሳ የሚይዘው በዚህ መንገድ ነው።

ነቀርሳ እጅ በመጨበጥ፣በልብስ፣በምግብ፣በሰሃን ወይም ዕቃ በመንካት ሊተላለፍ አይችልም።

**ድብቅ ነቀርሳ በሽታንም ሆነ ነቁ ነቀርሳ በሽታን ማከሚያ ጥሩ መድሃኒት አለ።**

**በድብቅ ነቀርሳ በሽታና በንቁ ነቀርሳ በሽታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**
አብዛኛውን ጊዜ የነቀርሳ ጀርሞች ሰውነት ውስጥ ሲገቡ "ይተኛሉ"። ይህ "**ድብቅ የነቀርሳ በሽታ**" ወይም "LTBI"ተብሎ ይታወቃል። "የተኙ" የነቀርሳ ጀርሞች ሰውነትዎንም አይጎዱም እርስዎንም አያሳምሙም። ድብቅ ነቀርሳ እስከ ብዙ ዓመት ሊቆይ ይችላል። ማንቱ የተባለውን የቆዳ ምርመራ አድርጎ ሰውነትዎ ውስጥ የነቀርሳ ጀርም መኖሩን ማወቅ ይቻላል።

"**ንቁ የነቀርሳ በሽታ**" የሚሆነው የነቀርሳ ጀርሞቹ ነቅተው ሰዉነትዎ ውስጥ ማደግና ሰውነትዎን መጉዳት ሲጀምሩ ነው። ንቁ የነቀርሳ በሽታ ያለባቸው ሰዎች በጣም ሊታመሙ ይችላሉ። የነቀርሳ ምልክቶች የማይለቅ ሳል፣ክብደት መቀነስ፣ምግብ አልበላ ሲል፣ማታ ማታ ሲያልብ፣ ትኩሳት እና የደረት ሕመም ናቸው። ነቀርሳው ሳንባ ውስጥ ከሆነ ያለው ወደ ሌላ ሰው ሊጋባ ይችላል።

የድብቅ ነቀርሳ ካለቸው ሰዎች አሥር በመቶው ወደ ንቁ **ነቀርሳ** ይቀየርባቸዋል። ሌሎች የጤና ችግሮች ካልዎት የመታመሙ ዕድል የባሰ ይሆናል።

# የነቀርሳ ተላላፊነት ምርመራዎች - ገጽ 2

**ነቁ የነቀርሳ በሽታ ከያዘኝ ቤተሰቤንና ጓደኞቼን የምከላከለው እንዴት ነው?**
ማድረግ ያለብዎት አራት አስፈላጊ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ***መድሃኒቶችዎን በተነገርዎት መሠረት መውሰድ፡፡*** የነቀርሳ መድሃኒቶችዎን መውሰድ ሲጀምሩ ዶክተርዎ መዲሃኒቱ በደንብ መስራቱን ለማረጋገጥ ሙከራዎች ያደርጋል፡፡ መዲሃኒቱ በቂ ጀርሞች ከገደለ በኂላ መድሃኒቱን ሳያቋርጡ መውሰድ መቀጠል አለብዎት ሆኖም ከዚህ በኂላ ነቀርሳን ለሰው አያጋቡም፡፡
2. **ነቀርሳን ማጋባት እስከማይችሉ ጊዜ ድረስ ሲስሉ አፍዎን በጨርቅ ይሸፍኑ፡፡**
3. የጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ የነቀርሳ ጀርሞችን ለሌላ ሰው ከማጋባት ለመቆጠብ በተጨማሪ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ይነግርዎታል/ትነግርዎታለች፡፡
    - ከሕዝብ መገልገያ ቦታዎች፣ከሥራ እና ከት/ቤት መገለል ይኖርብዎት የሆናል፡፡
    - እንግዶች ቤትዎ እንዳይመጡ ማስጠንቀቅ ይኖርብዎት ይሆናል፡፡
4. **የጤና ጥበቃ ሠራተኛውን/ዋን በተላላፊነት ምርመራው ላይ ያግዙት/ያግዟት፡፡** የጤና ጥበቃ ሠራተኛው/ዋ ቤተሰብዎንና ጓደኞችዎን ከነቀርሳ መከላከል ይፈልጋል/ትፈልጋለች፡፡

**አንድ የማውቀው ሰው ነቁ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ አለው፡፡ ይህን በተመለከተ ምን ማወቅ አለብኝ?**
ንቁ የነቀርሳ በሽታ ካለው ሰው ጋር ብዙ ጊዜ አብረው ካሳለፉ የነቀርሳ ጀርሞቹን ወደ ሰውነትዎ ውስጥ ተንፍሰው አስገብተው ሊሆን ይችላል፡፡ የነቀርሳ ምርመራ ማድረግ ለእርስዎ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ካስፈለገ የጤና ጥበቃ ክፍልዎ በነጻ የማንቱ የቆዳ ምርመራ እንዲያገኙ ያስደርግልዎታል፡፡

ከማንቱው የቆዳ ምርመራ **ነጻ** ከሆኑ ሰውነትዎ ውስጥ የነቀርሳ ጀርሞች የለብዎትም ማለት ነው፡፡  ይህንን ግን ለማረጋገጥ አንዳንድ ሰዎች ከተወሰኑ ሳምንታት በኂላ ድጋሚ ሌላ ምርመራ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

የማንቱ ምርመራው **እርግጠኛ** ከሆነ ሰውነትዎ ውስጥ የነቀርሳ ጀርሞች አሉ ማለት ነው፡፡ ድብቅ ነቀርሳ የሁን ንቁ ነቀርሳ ያለብዎት ላማወቅ ዶክተር ጋር መሄድና የደረት ራጅ መነሳት ይኖርብዎታል፡፡ ድብቅ ነቀርሳ ከሆነ ያለብዎት መድሃኒት በመውሰድ የነቀርሳ ጀርሞቹን መግደል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ወጣት ልጆች፣ኤችአይቪ የያዛቸው ሰዎች ወይም ሌላም ዓይነት የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች የንቁ ነቀርሳ የመያዛቸው ዕድል ከሌሎች ሰዎች የበለጠ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የማንቱ ምርመራቸው ነጻ ቢሆንም መድሃኒት መውሰድ ይኖርባቸው ይሆናል፡፡

የማንቱ ምርመራዎ ነጻ ቢሆንም የነቀርሳ ምልክቶች ካለብዎት (ለምሳሌ የማይለቅ ሳል፣ክብደት መቀነስ፣ማታ ማታ ላብ፣ምግብ አልበላ ሲል፣ትኩሳት፣የደረት ሕመም) ዶክተር ጋር መሄድ አለብዎት፡፡

**ከዚህ በፊት የማንቱ ምርመራ አድርጌ ዉጤቱ እርገጠኛ ከሆነስ?**
ከዚህ በፊት የማንቱ ምርመራ አድርገው እርግጠኛ እንደነበር የሚያሳይ ሰነድ ካልዎት ሌላ አያስፈልግዎትም፡፡ ሰነድ ከሌልዎት አሁን ሌላ ምርመራ መውሰድ ይኖርብዎታል፡፡ ይህ አይጎዳዎትም፡፡

**የቢሲጂ ክትባትን በተመለከተስ?**
ቢሲጂ ሁልጊዜ ከነቀርሳ አይከላከልዎትም፡፡ ቢሲጂ ሁልጊዜ የማንቱ ምርመራው እርግጠኛ እንዲሆን አያደርግም፡፡ የቢሲጂ ክትባት ቢኖርዎትም የማንቱ ምርመራ ማድረግ አይጎዳዎትም፡፡

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Tuberculosis Prevention and Control Program
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
1-877-676-5414
www.health.state.mn.us/tb

6/2005